# ግብፅ የአባይ ስጦታ ከሆነች፣ አባይ ደግሞ የኢትዮጵያ ስጦታ ነው!

**(በመለስ ዓ.)**

የቀድሞው የግብፅ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት «የአባይን ውሃ ፍሰት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ተግባር ግብፅን ወደ ጦርነት የሚያስገባና እና ጠንካራ የአፀፋ እርምጃን የሚጠይቅ ይሆናል።» ማለታቸው ተደጋግሞ ይገራል። የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና በኋላም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሀፊ የነበሩት ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊም ከእንግዲህ በኋላ በአለም የሚፈጠረው ጦርነት በውሃ ምክንያት እንደሚሆን በመግለፅ «ልብ ያለው ልብ ይበል» አይነት መልዕክት አስተላልፈዋል። እነዚህ የአባይ ውሃ ጉዳይ ለግብፅ የሞት ሽረት ጉዳይ ነው የሚል እንድምታ ያላቸው ንግግሮች ትናንት የተባሉ ናቸው። ዛሬም ግን የግብፅ ከፍተኛ ባለስልጣናት የአባይ ጉዳይ በተነሳ ቁጥር ተመሳሳይ ድምፀት ያላቸውን አስተያየት እየሰጡ ይገኛሉ። የሀገሪቱ የመስኖና የውሃ ሚኒስትሮች፣ የአገሪቱ ፓርላማ አፈ ጉባኤ፣ የግብርና ሚኒስትር … ወዘተ ተመሳሳይ አቋም አንፀባርቀዋል። የግብፅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቡል ጋይት ማንኛውም ወገን «ቀይ መስመሩን» ማለፍ የለበትም ሲሉ የአገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን ይህንኑ ተቀባብለው አናፍሰውታል። እዚህ ላይ የሚገርመው እኛው ኢትዮጵያውያን የአስተያየቶቹን ይዘትና አንድምታ ሳንፈትሽ ይህንኑ የግብፆች አስተያየት እንዲገደል ማሚቱ ማስተጋባታችን ነው። የአባይን ውሃ እስከዛሬ ያልተጠቀምነው ከግብፅ ተፅዕኖ በተጨማሪ በራሳችን ችግር መሆኑን ልንቀበል አለመቻላችን ይገርማል።

ከግብጽ ሰሞኑን በተለያየ መልኩ በተከታታይ እየወጡ ያሉትን መግለጫዎች በተወሰኑ ሀገሮች በቅርቡ ከተፈረመው የናይል ስምምነት ጋር በማያያዝ ጦርነት አይቀሬ ነው እስከማለት የደረሱ ወገኖች አልታጡም። አንዳንድ የአገራችን ጋዜጦችም የፍጻሜው መጨረሻ መቃረቡን ጠቅሰዋል። በውጭ ሀገር የሚገኙ ድረ-ገጾችም «እንግዲህ ይዋጣልን» በሚል የኢትዮጵያውያን አትንኩን ባይነት፣ ጀግንነት ከመቶ ዓመት በላይ ወደኋላ በመሄድ በመጥቀስ መቀኘትና መጻፍ ጀምረዋል። እንደዚህ ፀሀፊ እምነት በግብፅ ባለስልጣናት፣ ምሁራን እንዲሁም ጋዜጦች የተሰጡት መግለጫዎች ቀደም ብሎ ሲሉት የነበረ እንጂ ምንም አዲስ ነገር የለውም። በቅርቡ ከተፈፀመው ስምምነት ጋር ተያያዥ ሆኖ እንደ አዲስ ነገር የሚነሳ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ግብፅ ያለ አባይ ምንም ናትና አካኪ ዘራፍ ቢሉ ግብጾችን ልንረዳቸው ይገባል። የመገናኛ ብዙሃን ህብረተሰቡ የተሟላ ግንዛቤ በጉዳዩ ላይ እንዲኖረው ለማድረግ የመጣራቸው ሁኔታ አንድ ነገር ሆኖ በጉዳዩ ዙሪያ ያሉትን አባባሎች ከሚገባው በላይ በመለጠጥ ማስጮህ ግን ተገቢ መስሎ

አይታየውም። ምክንያቱም የግብፅን መሠረታዊ ጥቅም የሚጎዳ ምንም ነገር አልተፈፀመም፤ የመፈፀሙም ፍላጎት አገራችን የላትም። የአሁኑ የግብፅ መግለጫና አስተያየት ዋና ምክንያት የአባይ ውሃ ወይም የተፈረመው ስምምነት ሳይሆን የሀገሪቱ ወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶች ነፀብራቅ ነው።

## አባይ አባይ ያገር ሲሳይ

ስለ አባይ ብዙ ተቀኝቷል ተዘፍኖለታል። የተፋሰሱ አገሮች ጉዳዩን እንደኛው ስለመያዛቸው በግልጽ መናገር ቢቸግርም የትሩፋቱ ተጠቃሚ አለመሆናቸው እንደሚያንገበግባቸው ግን መናገር ይቻላል። ዘ-ስታንዳርድ የተባለ የኬንያ ጋዜጣ በተወሰኑ የናይል ተፋሰስ አገሮች መሀከል ዩጋንዳ ውስጥ ስምምነት ከተፈረመ በኋላ «ስምምነቱ እንኳን ተፈረመ እንጂ ዛፍ መትከል እንጀምራለን» ማለታቸውን የዘገበ ሲሆን ይህን አስተያየት በተፋሰሱ አገሮች ያሉ ህዝቦች ይጋሩታል ብዬ እገምታለሁ።

ይህ ምኞት እንዳለ ሆኖ የናይልን ውሃ ጥቅም ላይ ለማዋል ከተናጠል ጥረት ይልቅ የጋራ ርብርብ ለማድረግ የተሞከረበት ወቅት አልነበረም። ተፋሰሱ ከአፍሪካ የቆዳ ስፋት አንድ አስረኛውን የሚሸፍን፣ 300 ሚሊዮን ህዝብ በአካባቢው የሚኖርበት፣ በተፈጥሮ ፀጋ የታደለ ቢሆንም ብዙም ጥቅም ላይ አልዋለም። የተፋሰሱ አገሮች ይህን ለማድረግ ያልታደሉት የመጀመሪያው ምክንያት የግብፅና የሱዳንን «ታሪካዊ መብት» ያስከበረ የቀኝ ገዥዎች ዘመን ስምምነት ሰለባ በመሆናቸው ነው። በሁለተኛ ደረጃ በላይኛው ግርጌ አገሮች ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሳይኖር በመቆየቱና ኢኮኖሚያቸውም በውሃው ላይ ሊካሄድ የሚችልን ልማት መሸፈን ሳይችል በመቆየቱ በኢትዮጵያና ሌሎች የተፋሰሱ አገሮች በኩል ይቀርብ የነበረው የፍትህና የእኩል ተጠቃሚነት ጥያቄ ተቀባይነት ሳይኖረው ቆይቷል። ይህ ለአንድ ወገን ያደላ ስምምነት ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ የተለያዩ ሀገሮች ለግብፅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ማድረጋቸው ሌላው ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። ግብፅ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ እና በአረቡ ዓለም ባላት ተሰሚነት ሳቢያም ሌሎቹ አገሮቹ ውሃውን ተጠቅመው ለልማታቸው ብድር እንዳያገኙ በማድረግ የተሳካ ስራን የሰራች ሲሆን በአንፃሩ የተፋሰሱ አገሮች ለዚህ የሚመጥን የአፀፋ እርምጃ ለመውሰድ የነበራቸው አቅም አናሳ ነበር። እነዚህ ተፅዕኖዎች ሳይሰሩ ሲቀር ቀደም ሲል እንደተገለፀው በናይል ላይ የመጣ በአይናችን የመጣ በሚል ወታደራዊ እርምጃ እወስዳለሁ በማለት ማስፈራራቱ የተለመደ ነበር። በተለይም ባለፉት 100 ዓመታት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከግብጽ ጋር ከፍጥጫ የተለየንበት ጊዜ የለም።

ለወደፊት ከኢትዮጵያ ጋር ሊደረግ ይችላል ለተባለ ውጊያ ግብፅ በጫካ/ በተራራ ውጊያ የሰለጠነ ጦር እንዳዘጋጀች ሲወራ ቆይቷል። ከማስፈራራት በዘለለ ወደ ቀጥታ ፍጥጫ መግባት አለመግባቷ አንድ ነገር ሆኖ የቀድሞ የግብጽ የመከላከያ ሚኒስትር ሌተናል ጄኔራል መሀመድ ሁሴን ታንታዊ የግብፅ ወታደራዊ ስትራቴጂ በናይል ላይ ከሚካሄድ ጦርነት ጋር የተቃኘ እንደሆነ በግልፅ አስረግጠው ተናግረዋል።

ከዚህ የግብፅ ማስፈራሪያ በመለስ በተፋሰሱ አገሮች መሀከል የሚካሄደው የትብብር መንፈስ ከአስርት ዓመታት በላይ የዘለለ ዕድሜ የለውም። የአፍሪካ ቀንድ ጉዳይ ተመራማሪ የነበሩት ፕሮፌሰር ክንፈ አብርሃ የግጭትና የትብብር ታሪክ ባለው ናይል ላይ ወደ ትብብር የመቅረብ አዝማሚያ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1967 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አማካኝነት የውሃና የአባይ ጠባይ መረጃ በማሰባሰብ እንደሆነ ይጠቀሳሉ። ከዚያ በመቀጠል በ1993 የናይል ተፋሰስ የልማትና የአካባቢ ጥበቃ የቴክኒክ ትብብር፣ በካናዳ ኢንተርናሽናል የልማት ድርጅት (ሲዳ) አማካኝነት፣ በ1997 በአለም ባንክ ድጋፍ የተጀመረው የናይል ተፋሰስ አገሮች የትብብር ጥረቶች ተጠቃሽ ናቸው።

የአባይ ተፋሰስ አገሮች ወደ አዲስ የትብብር መንፈስ መግባት የጀመሩት በአካባቢው አገሮች አንፃራዊ ሠላም በመረጋገጡና ይህን ተከትሎ የኢኮኖሚ ዕድገት በማሳየታቸው ነው። በዚህም ሳቢያ አገሮቹ ናይልን ለኃይል ምንጭ፣ ለመስኖ እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች የመጠቀም ፍላጎት እና ቁርጠኝነት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋርም አገሮቹ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ለነገ የማይሉት ጉዳይ ሆኗል። እነዚህ የተፋሰሱ አገሮች አባይን፣ ቪክቶሪያን፣ አልበርትን እና የኤድዋርድ ሃይቆችን ይዘው የእገሌን ልጅ ውሃ ጠማው ማለት አልነበረባቸው እና ከጥቂት ዓመታት በፊት የጀመሩት ጉዞ ፈር ይዟል። ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ.ም ኢትዮጵያ፣ ዩጋንዳ፣ ታንዛኒያ እና ሩዋንዳ ኢንቴቤ ውስጥ የናይል ስምምነቶችን ሲፈራረሙ ኬንያም ከጥቂት ቀናት በኋላ ተቀላቅላለች። ቡሩንዲ እና ዲሞክራቲክ ኮንጎ ለአንድ ዓመት ክፍት የሚሆነውን ስምምነት ይፈርማሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በናይል ተፋሰስ የታዛቢነት መቀመጫ ያላት ኤርትራ ግን ስምምነቱን አልደግፍም ብላለች። ይህ የሱዳን እና ኤርትራ አቋም ከምክንያታዊነቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ጎኑ ያመዝናል። ምክንያቱም የኢኒሼቲቩ 10ኛ ዓመት እ.ኤ.አ 2007 ታንዛኒያ ውስጥ ሲከበር የሱዳን የውሃ ሃብትና መስኖ ሚኒስትር አገራቸው በፍትሃዊ ክፍፍል እንደምታምን በግልፅ አስቀምጠዋልና ውሳኔው የግብጽ ጫና አያጣውም አሰኝቷል። ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂም ኤርትራን ሳይቀር አንድ የጠርሙስ ውሃ የሚከለክለውን የድሮ ስምምነት መቀበላቸው ራሳቸው ግብዖችን ቢያስገርምም አቶ ኢሳያስ ኢትዮጵያ

የደገፈችውን የመቃወማቸው አባዜ አለቀቃቸውም:: አዋቂ የሚባለው የኤርትራ ድረ-ገጽ ግብፅ በኤርትራ ወታደራዊ የጦር ሰፈር እንድትከፍት ፕሬዚዳንቱ መጠየቃቸውን ዘግቧል::

ይህ አሁን የተደረሰው ስምምነት ቢያንስ በስድስት ሀገሮች ተፈርሞ ወደየሀገሮቹ ፓርላማ ሄዶ ከፀደቀ የአፍሪካ ህብረትም እንዲያውቀው ይደረጋል:: ከዚህ በፊት ግብፅ የኬንያን ጠቅላይ ሚኒስትርና የኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንትን ካይሮ ጠርታ ያነጋገረች ሲሆን የቡሩንዲ መሪም ተጋብዘዋል:: በቀጣይ ስምምነቱ ለየሀገሮቹ ፓርላማ ከቀረበ ውሉ እንዳይጸድቅ በአረቡ ዓለም ብሎም በምዕራባውያን ሸሪኮቿ በኩል ግብፅ ተፅዕኖ ለማድረግ ትንቀሳቀሳለች:: የዚህ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ግብ የተፋሰሱን አገሮች ህብረት በመበተን ፍትሃዊ ያልሆነውን ስምምነት ማስቀጠል ነው:: የኢንቴቤው ውል የናይል ተፋሰስ አገሮችን የውሃ አጠቃቀም፣ ልማት፣ እንክብካቤ እንዲሁም የተፋሰሱን አገሮች አጠቃላይ መብትና ግዴታ የሚወስን ነው:: እያንዳንዱ አባል አገር ምን ያህል መጠን ያለው ውሃ ሊደርሰው እንደሚገባም ወደፊት ይታወቃል:: ይህ ስምምነት በተፋሰሱ አገሮች ውስጥ አዲስ ተስፋን ፈንጥቋል:: የታንዛኒያው ምክትል ፕሬዚዳንት አሊ መሀመድ ሼን ከስምምነቱ መፈረም በኋላ እንዳሉት የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ ብዙ ፈተናዎች ቢቀሩትም ጥርጣሬ እና ስጋት የተሞላበትን ድባብ ለመቀየር ስምምነቱ ጠቃሚ ነው::

ከተፋሰሱ አገሮች በተቃራኒ የግብፅ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና የመገናኛ ብዙሃን እንደተለመደው ሁሉ ከዛሬ 30 ዓመት በፊት የነበረውን መፈክር እና ማስፈራራት ነው ሲያሰሙ የከረሙት:: እንዲያውም አንድ የግብጽ ከፍተኛ ባለስልጣን አል-ታያር ለተሰኘ ጋዜጣ በሰጠው መግለጫ «ግብጽ ተገዳ ወደወታደራዊ እርምጃ ልትገባ ትችላለች፤ ኢትዮጵያንም በሱዳን፣ በሶማሊያ ወይም በኤርትራ በኩል ልታጠቃ ትችላለች» ብለዋል:: በኬኩ (ናይል መሆኑ ነው) ላይ ከመጣላት «ኬኩን እናሳድገው» የሚሉት ግብፆች ከክፍፍሉ በፊት የጋራ ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ ስምምነት በመፈረሙ ድንጋጤ ነው የተሰማቸው:: ከላይ የተገለፀው ማስፈራሪያ እንዳለ ሆኖ ሁኔታውን በሰከነ መንፈስ መከታተል ያስፈልጋል:: ዩኔስኮ ያሳተመው አንድ ጥናት እንደሚያመላክተው ከጤግሮስ እስከ ኤፍራተስ ከናይል እስከ ዳንዩብ ወንዞች/ተፋሰሶች ባለፉት አምስት ሺ ዓመታት በጥንታዊቷ ኢራቅ የኡማ እና አካክ የከተማ መንግስታት ከተካሄደው ውጭ ምንም ጦርነት በውሃዎቹ ምክንያት አልነበረም::

## ግብፅ የአባይ ስጦታ

ለበርካታ ግብፃውያን የኢንቴቤው ውል በአገራቸው ደህንነትና ህልውና ላይ የተጋረጠ አደጋ አድርገው ነው ያቀረቡት፡፡ ፕሮፌሰር ክንፈ አብራሃ እንደጻፉት የግብጽ መንግስታት በአባይ ላይ የሚያራምዱት አቋም ሰነልቦናዊ ነው፡፡ ግብፆች አባይን ሲያመልኩ ቆይተዋል፡፡ ግብፅ የአባይ ስጦታ ናት ሲል ሄርዱቶስ ከአምስት ሺህ ዓመተ ዓለም በፊት የሰጠው ስያሜ ከደማቸው ጋር ተዋህዷል፡፡ ፒ. ጎድይሬይ ኦክት የተባሉ የማህበረሰብ ጥናት ተመራማሪ ናይል የትብብር ሳይሆን የጥላቻ መንስኤ የሆነው ግብፅ «በውሃ እጥረት ስጋት/ፍርሃት /Water stress phobia/ ስለምትሰቃይ እንደሆነ በመግለፅ የስሜቱን ጥንካሬ ያሳያሉ፡፡

ታዋቂው የግብጽ ፈላስፋ ዶ/ር ጋማል ሃማዳን ግብጽ በአፈሯ እና ውሃ እንጂ አፍሪካዊ በደም እና በዘር ግን አውሮፓ ናት የሚለውን አባባላቸውን ብዙዎች ይናገራሉ፡፡ አንዳንድ ግብፃዊያን ተንታኞች አገራቸው በናይል ላይ ያላት የማይገሰስ መብት የተደፈረው አገራቸው አፍሪካ በመተው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ፣ አውሮፓና አሜሪካ በማተኮሯ ነው ሲሉ ይከሳሉ፡፡ በተለይም ከ1980ዎቹ ወዲህ ግብፅ በአፍሪካ የነበራት ሚና እየደበዘዘ መምጣቱን ለእስራኤል-ፍልስጤም ውዝግብ መፍትሄ አማጭነቷም እየቀነሰ መምጣቱን ይጠቅሳሉ፡፡ ፕሬዚዳንት ሙባረክ አዲስ አበባ ውስጥ በአሸባሪዎች ከተቃጣባቸው የግድያ ሙከራ በኋላ በአፍሪካ አንድነትና ህብረት ያላቸው ተሳትፎ የጎላ አይደለም፡፡ ከግብፅ ይልቅ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ መድረኮች ያላት ተስማሚነት እየጎላ መምጣቱን በግብፅ የአል አህራም የፖለቲካ እና ስትራቴጂክ ጥናት ማዕከል ተመራማሪ ነቢል አብዱልፈታህ ገልፀዋል፡፡ የአካባቢው አገሮች በኢኮኖሚ እያደጉ መምጣታቸውንም ተመራማሪው በአፀንኦት ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በከረረ መልኩ የናይልን ጉዳይ ከውሃ ደህንነት ይልቅ ጂኦ-ፓለቲካዊ እንድምታ እንዳለው የሚገልፁም አልጠፉም፡፡ እነዚህ ወገኖች እስራኤል ወደተፋሰሱ ሀገሮች ሰርጋ ገብታ ታማክራለች ብለው ይገምታሉ፡፡ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር በመሆን የግብፅን ብሄራዊ ጥቅም የሚጎዳና በመካለኛው ምስራቅ ያላትን ሚና የሚያሽመደምድ ተግባር እየፈፀመች ነው፤ ለዚሁም የእስራኤል የስለላ ድርጅት ሞሳድ በአፍሪካ ትልቅ ጽ/ቤቱን አዲስ አበባ ከፍቷል ይላሉ፡፡ አሜሪካም ብትሆን ደቡብ ሱዳኖች ቢገነጠሉ ብዙም ቅር ላትሰኝ ስለምትችል በተፋሰሱ ሌላ 10ኛ አገር ይፈጠራል፣ እንደ ሶማሊያ ወደብጥብጥ ከገቡ ደግሞ ብሄራዊ ጥቅሜ ይጎዳል፤ ይባስ ብሎ የኑባ ግዛት ከግብጽ ልትገነጠል እንደምትችል በመግለጽ የግብፅ የህልውና አደጋ /Existential Threat/ የሚፈጠረው በናይል እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡፡

ከእነዚህ አስተያየቶች በተቃራኒ ጥቂት ቢሆኑም አንዳንድ ምሁራን ግብፅ በአካባቢው ከነባራዊ ሁኔታው ጋር በመታረቅ የተሻለ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይገባታል የሚል አቋም አሁን አሁን እያሳዩ ነው፡፡ በካይሮ ዩኒቨርሰቲ የጂኦግራፊ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶ/ር ሰዓድ ኢብራሂም ኤል-ባዳዊ ግብጽ ከናይል ተፋሰስ አገሮች ከሚያለያያት ይልቅ የሚያገናኛት ጉዳይ ስለሚበዛ በፖለቲካውና ፀጥታው መስክ አገራቱ የተረጋጉ እንዲሆኑ መስራትና በተለያዩ የልማት መስኮች ኢኮኖሚያዊ ትብብር ማድረግ ይኖርባታል ይላሉ፡፡ ፕሮፌሰሩን የመሰሉ ልህቃን ለናይል ወንዝ ጠብታ ውሃ የማታበረክተው ግብፅ 86 በመቶ ስትጠቀም 85 በመቶ የሚሆነውን ውሃ የምትለግሰው ኢትዮጵያ ድህነት ሲያንቃት የምትጠጣው ውሃ አይገባትም ማለት ኢ-ፍትሃዊ እና ኢ-ሞራላዊ ነው ቢሉም ለብዙ ሺህ ዘመናት የነበረውን የተዛባ አመለካከት መቀየር መቻላቸው ያጠራጥራል፡፡

<u>ምርጫ-በኢትዮጵያና ግብጽ</u>

ኢትዮጵያና ግብጽ ባለፈው ግንቦት ወር ምርጫ አካሂደዋል፡፡ በአገራችን ለአራተኛ ጊዜ በተካሄደው ምርጫ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባይን ጨምሮ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን አጀንዳ አድርገው ተከራክረዋል፡፡ ኢህአዴግ የአገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም እንዳላስከበረ በመግለፅ ተቃዋሚዎች ሲከሱት ገዢው ፓርቲም በአገር ጥቅም ላይ እንደማይደራደር ሲገልፅ ነበር፡፡ በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከአልጀዚራ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ አባይን በተመለከተ መፍትሄው ሁሉም ወገን ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ በዲፕሎማሲያዊ ድርድር ዕውን ማድረግ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ ግብፅ እኛ እየበላን እናንተ ተመልከቱ የሚለው አቋሟ ተቀባይነት እንደሌለውም አስምረውበታል፡፡ ይህን በኢትዮጵያ የተካሄደ አጠቃላይ ምርጫ የግብፅ ፖለቲከኞች በአንክሮ ሲከታተሉ እንደነበር አል አህራም ጋዜጣ ጠቅሶ ለየትኛውም ወገን የሰጡት ድጋፍ ግን የለም ብሏል፡፡

ግብፅ በበኩሏ ግንቦት 6 2002 ዓ.ም ለሀገሪቱ ሹራ ምክር ቤት /Shura Council/ ምርጫ ስታካሂድ ፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ የሚመሩት ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ፣ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና የግል ተወዳዳሪዎች በምረጡኝ ቅሰቀሳቸው ወቅት ዋነኛ አጀንዳቸው የነበረው ይኸው በቅርቡ የተፈረመው የናይል ውሃ ስምምነት ነበር፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ በህግ የታገደ በመሆኑ የእሱ አቀንቃኝ የሆኑ የግል ዕጩዎች እና ሌሎች ተቃዋሚዎች ገዢው ፓርቲ

ናይልን አሳልፎ እንደሰጠ አድርገው ሲቀሰቅሱ ነበር። አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ድረ-ገፆች እና ጋዜጦችም ይህን አስተጋብተዋል። እነዚህ ድረ-ገፆች ኢትዮጵያ 35 ግድቦችን ለመስራት ተዘጋጅታለች (እንደአፋቸው ያድርግልን)፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ግብፅን አስጠነቀቁ በማለት በሬ ወለደ ዜና ሲያስደምጡ ከርመዋል። አንዳንድ ግብፃውያን ተንታኞች የኢንቴቤው ውል መፈረም እንዲሁም የጣና በለስ ግድብ ግብፅ ውስጥ ከተካሄደው ምርጫ ጋር በተመሳሳይ ቀን መመረቁ የአጋጣሚ ነገር ወይንስ በኢትዮጵያ መንግስት ሆን ተብሎ የተከናወነ ድርጊት ነው እያሉ ሲጠይቁ ከርመዋል።

**<u>አልጋው መቼ ይረጋል?</u>**

የግብፅ ፓለቲካን የወደፊት ዕጣ ፈንታን በተመለከተ ማንም ወገን በእርግጠኛነት መናገር የማይችልበት ሁኔታ ላይ ነው። ግንቦት 6 ቀን 2002 ዓ.ም ለሹራ ምክር ቤቱ በተደረገው ምርጫ ገዢው ብሔራዊ ዲሞክራቲክ ፓርቲ (ኤን-ዲ-ፒ) ከ88 መቀመጫ 80፣ የቀድሞ የሙስሊም ወንድማማቾች አቋም አቀንቃኞች ምንም ባያገኙም ሌሎች ስምንት ፓርቲዎች ደግሞ ቀሪዎቹን መቀመጫዎች ማሸነፋቸው ለአብዛኛው ተራ ሰው ዕፎይታን ቢፈጥርም የሀገሪቱ ፖለቲካ በመስቀለኛ መንገድ ላይ ይገኛል። የፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ ዕድሜ ተጨምሮበት አስተማማኝ የጤንነት ሁኔታ ውስጥ አይደሉም ይባላል። ፕሬዚዳንቱን ማን ይተካል? የሚለው የሁሉም ራስ ምታት ሆኗል። ይሁን እንጂ የግብፅ ፖለቲከኞች ይህን ያልጠራ የስልጣን ሽግግር ጭንቀት ከናይል ወንዝ ጋር አያይዘው በሚያወጧቸው መግለጫዎች ህዝቡ አትኩሮቱን እንዲቀይር በማድረግ ሥልጣናቸውን ማደላደል ይፈልጋሉ እየተባለ ነው። መሀመድ አቡ ኤልጋሃር የተባሉ ጸሃፊ «የግብፅ ባለስልጣናት እያስጨነቃቸው ያለው ነገር የራሳቸው ጉዳይ ነው። ናይል ቢደርቅ እንኳ ግድ የላቸውም» ሲሉ ፅፈዋል።

ፕሬዚዳንት ሙባረክ በቅርቡ ጣሊያን ውስጥ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከጋዜጠኞች የቀረበላቸው ጥያቄ አልጋ ወራሹ ማን ይሆናል? የሚል ነበር። ፕሬዚዳንቱ ማን እንደሚተካቸው እሳቸውም እንደማያውቁ ገልጸው ፈጣሪ የቀባውን እኔም እመርጣለሁ ማለትን መርጠዋል። ይህ አስተያየት ሀገሪቱ ከፕሬዚዳንቱ አመራር ውጭ ለ30 ዓመት ለማያውቋት ግብጻውያን ታላቅ ድንጋጤ ነው። ፕሬዚዳንት ሙባረክ በገዢው ፓርቲ ቁልፍ ቦታ ያለው የ46 ዓመት ወንድ ልጃቸው ጋማል ሙባረክ ስልጣን እንዲረከብ ይፈልጋሉ ቢባሉም ከሀገሪቱ የመከላከያ፣ የደህንነት፣ የፖሊስ እና የፀጥታ ተቋሞች በኩል ድጋፍ እንደሌለው ይነገራል። ጋማል ሙባረክ በሙስና ስለሚታሙም ህዝቡ ስለማይፈልጋቸው ተቀባይነት የላቸውም። ይህ ካልሆነ ሙባረክ ራሳቸው

ለመቀጠል ይገደዳሉ የሚሉ ወገኖች አሉ። ሌሎች ደግሞ ለገዢው ፓርቲ አንድ ቀሪ ካርድ የሚሆኑት የሀገሪቱ የደህንነት ጉዳዮች ኃላፊ ናቸው። አምር ኤል-ሸባኪ የተባሉ የአረብ መድረክ ተቋም ኃላፊ በእስካሁኑ ሂደት ገዥው ኤን-ዲ-ፒ ሁሉንም የሚያስማማ ዕጩ አጥቶ እየዋለለ ነው ማለታቸውም የሚጣል አስተያየት አይደለም። ተቃዋሚዎችስ?

ግብፅ እ.ኤ.አ ከ1968 ጀምሮ የተገደበ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ታራምድ እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድም ጊዜ ለስልጣን አልበቁም። ጽንፈኞች የሚበዙበት የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ከ25 ዓመት በፊት በመታገዱ 1997 በተካሄደ ምርጫ በግል የቀረቡ ዕጩዎችና ተቃዋሚዎች ከሀገሪቱ ፓርላማ ያሸነፉት ሰማንያ መቀመጫ ብቻ ነው። ግብፅ በቁጥር 24 የተቃዋሚ ፓርቲዎች ይኑሯት እንጂ በውስጥ ዲሞክራሲ እጦት አንዳንዶቹም በአንድ ግለሰብ በዕርስትነት የሚመሩ በመሆናቸው ለህዝቡ ካብ አይገባ ድንጋይ ሆነው ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ግብፃውያን ዘንድሮ ተስፋቸውን በአንድ ሰው ላይ ጥለዋል መሀመድ ኤልባራዲ። የአለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ኃላፊ የነበሩት አልባራዲ ብሄራዊ የለውጥ ማህበር /National Association for Change/ የሚል ድርጅት በመመስረት የተበታተኑ ተቃዋሚዎችን ለማሰባሰብ እየሞከሩ ናቸው። አልባራዲ ከ25 ዓመት በፊት የታገደውን የሙስሊም ወንድማማቾች ድርጅት አመራሮች ጨምሮ የበርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ድጋፍ አግኝተዋል። ምሁራን፣ ተማሪዎች እና ልህቃንም ከጎናቸው እንደማይለዩ እየተናገሩ ናቸው። በግብፃውያን ዘንድ የመነቃቃት መንፈስ የፈጠሩት አልባራዲ ካላቸው ዲፕሎማሲያዊ ብቃት፣ በዓለም አቀፍ መድረኮች ያላቸውን ተሰሚነት/ተቀባይነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ጠቃሚ ናቸው ያሏቸውን ሰባት ነጥቦች አስቀምጠዋል። ከእነዚህም ዋነኞቹ በሀገሪቱ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ የዘለቀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ይነሳ፣ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ይመቻቹ፣ የግል ዕጩዎች ለፕሬዚዳንትነት እንዲወዳደሩ ይፈቀድ የሚሉት ናቸው። ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ህገ መንግስት መሠረት አልባራዲ ለፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በግል ለመወዳደር ከሀገሪቱ ሴኔትና ፓርላማ የ230 እንደራሴዎችን የድጋፍ ፊርማ ላያገኙ ይችላሉ። የፓርቲዎች ጥምረትን የሚወክሉ ቢሆኑም ሙባረክ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተጨማሪ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት በማራዘማቸው አሸናፊነታቸውን ለማረጋገጥ ያስቸግራቸዋል። የተቃዋሚ ጥምረት ዕጩ ሆነው ቢቀርቡ የሀገሪቱ የፀጥታ መዋቅሮችን ድጋፍ ስለማያገኙ ባይመረጡም አልባራዲ በምርጫው ሙባረክ ሰፊ የማሻሻያ ዕርምጃ እንዲወስዱ ምክንያት ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ ፖለቲካዊ ሽግግር ውጥረት በተጨማሪ የግብፅ ባለስልጣናት የናይልን ጉዳይ ይዘው ያራግቡ እንጂ በሀገሪቱ ሰፊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የከፋ ደረጃ ላይ መድረሳቸው ይነገራል፡፡ አርባ በመቶ የሚሆነው ህዝቧ በድህነት ውስጥ በሚገኘው ግብፅ ለዳቦ ሰልፍ መውጣት የተለመደ እየሆነ መጥቷል፡፡ የስራ አጥ ቁጥሩ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ፤ የትምህርትና የጤና ተቋማት ክፉኛ መዳከማቸውም ብዙ ወገኖች «ለወጥ» እንዲሉ ገፍቷቸዋል፡፡ ባለስልጣናቱ በናይል ጉዳይ ብዙም የታየ ለውጥ ባይኖርም አገሪቱ አሁን ያለችበትን ማዕበል ቀዝፋ መውጣት እንድትችል የሰሞኑን ስምምነት የብሔረተኝነት ስሜት መፍጠሪያ መንገድ እያደረጉት እንደሆነ በሰከነ መንፈስ መረዳት ይገባል፡፡ ስለሆነም እኛም አላስፈላጊ እሰጣ ገባ ውስጥ በመግባት ለዘብተኛ አቋም እያሳዩ የመጡ ጥቂት ግብፃውያንን ወደ ፅንፍ ማስገባት አይገባንም፡፡ ኢትዮጵያ አሁን የጀመረችውን የልማት ግስጋሴን የሚቀለብስ ሁኔታ ለማስተናገድ ጊዜ የላትምና፡፡

ኢትዮጵያውያን በምንም ጉዳይ ያላቸውን ልዩነት ተሻግረው በአባይ ጉዳይ እንደ አንድ ሰው መናገር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በእስካሁኑ ሂደት የኢትዮጵያ መንግስት ከሌሎች አገሮች ጋር በመሆን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የሄደበት ርቀት በአባይ ጉዳይ ላይ አዲስ ምዕራፍ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባይን በተመለከተ ለመንግስት ድጋፍ መስጠታቸውም ተገቢ እርምጃ ነው፡፡ የመጨረሻው ግብ አልተደረሰምና መፈንደቅም፣ ማዘንም፣ መፎከርም፣ መቆጣትም ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ግብጽ የናይልን ስጦታ ናት፡፡ የዛኑ ያህል አባይ ኢትዮጵያ ለዓለም ካበረከተቻቸው ጸጋዎች አንደኛው ነው፡፡ የናይል ጉዳይ የያዘው ዶሴ ተገቢውን ፍትህ እንዲያገኝ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱን ከመቀጠል ውጭ የቃላት እንካሠላንታ ውስጥ መግባት የሌላውን ወገን ካርታ መጫወት ነው፡፡ ናይል የስሌት እንጂ የስሜት ጉዳይ መሆን የለበትም፡፡ ከዚህ ፀጋ ተቋዳሾች ጋር በጋራ ጠቀሜታ ላይ የተመሠረተ ትብብር በማድረግ አባይን የልማት እንጂ የጥፋት መንስኤ እንዳይሆን ማድረግ ይገባል፤ ይችላልም፡፡